# 13ኛው የኢትዮጵያ ግማሽ ማራቶን ውድድር

# ሕግና ደንብ

## የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

ጥር 24/2012

ኦሮሚያ ቢሾፍቱ

# 13[ኛው] የኢትዮጵያ ግማሽ ማራቶን ውድድር
# አጠቃላይ መረጃ

- የውድድሩ ቀን፡- ጥር 24/2012 ዓ.ም.
- የውድድሩ ቦታ፡- ኦሮሚያ ቢሾፍቱ
- የውድድሩ ተሳታፊዎች፡- ክልል፣ከተማ አስተዳደሮች፣ ክለቦች፣ ማዕከላትና ተቋም
- አዘጋጅ፡- የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

## <u>አድራሻ</u>


- ፖ.ሣ.ቁ 13336
- ፋክስ 251-11-6450879
- ኢ-ሜል eth@mf.iaaf.org
- Website www.eaf.org.et

- ☎ 251-11-6479579
  251-11-6479676
  251-11-6479596
  251-11-6479131
  *ጉርድ ሾላ*
  *<u>አዲስ አበባ</u>*


## <u>ጥቅል ፕሮግራም</u>

- *ጥር 23/2012 ዓ.ም. የቴክኒክ ስብሰባ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ቢሾፍቱ ወጣት ማዕከል*
- *ጥር 24/2012 ዓ.ም. ውድድሩ የሚካሄድበት ቀን፤*

# 13ኛው የኢትዮጵያ ግማሽ ማራቶን ውድድር

# ሕግና ደንብ

**የውድድሩ ዓላማ**

1. ለክልሎች ከተማ አስተዳደሮች፣ ክለቦችና ተቋማት አትሌቶች የጐዳና ላይ ሩጫ ውድድር ዕድል ለመፍጠር፤
2. በአገር ውስጥ የውድድር ልምድ እንዲያዳብሩ እንዲሁም ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት፤
3. በክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮችና ክለቦች መካከል ጤናማ የውድድር መንፈስ ለመፍጠር፤

## *አንቀጽ አንድ*

## *አጠቃላይ የውድድር ደንብ*

1. **የውድድሩ ስያሜ፡**- ይህ ውድድር 13ኛው የኢትዮጵያ ግማሽ ማራቶን ውድድር ተብሎ ይጠራል፡፡
2. **ውድድሩ የሚመራው**፡- ይህ ውድድር በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንና በIAAF ሕግና ደንብ መሠረት ይመራል፡፡

## *አንቀጽ ሁለት*

## *ቡድኖች የሚያስመዘግቡት ተወዳዳሪዎች ብዛት*

ማንኛውም ተወዳዳሪ ክልል ፣ ከተማ አስተዳደር፣ ክለብና ተቋማት በእያንዳንዱ ጾታ ከአራት/4/ እስከ አስራ ሁለት/12/ አትሌቶች ብቻ ማስመዝገብ ይችላሉ፡፡ ከአራት አትሌት በታች ከሆኑ በግል እንጂ እንደ ቡድን ሊወዳደሩ አይችሉም፡፡

## *አንቀጽ ሦስት*

## *የውድድሩ ቀንና ቦታ*

13ኛው የኢትዮጵያ ግማሽ ማራቶን ውድድር ጥር 24/2012 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል ቢሾፍቱ ከተማ ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል፡፡

## *አንቀጽ አራት*

## *የዕድሜ ገደብ*

ማንኛውም የግማሽ ማራቶን ተወዳዳሪ አትሌት ቢያንስ ዕድሜው 18 ዓመት የሆነው ማለትም (በ1994 ዓ.ም. ወይም እ.ኤ.አ በ2002) እና በኋላ የተወለደ መሆን አለበት፡፡ ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ተወዳዳሪ በውድድሩ መሳተፍ አይችልም፡፡

## *አንቀጽ አምስት*

## *የምዝገባ ጊዜ*

የምዝገባ ጊዜ ጥር 4-15/2012 ዓ.ም. እስከ 11፡00 ሰዓት ድረስ ጉርድ ሾላ በሚገኘው የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡ የምዝገባ ቀን ያሳለፈ ተሳታፊ ቡድን *300.00 ብር / ሶስት መቶ ብር/* በመክፈል ጥር 18/2012 ዓ.ም. ብቻ እስከ ቀኑ 11፡00 ሰዓት ድረስ መመዝገብ ይችላል፡፡

## *አንቀጽ ስድስት*

## *የውድድሩ ተሳታፊዎች*

በውድድሩ በሁለቱም ጾታ ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ ክለቦች፣ ተቋማትና የግል ተወዳዳሪዎች ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

## *አንቀጽ ሰባት*

## *በስም ጥሪ ቦታ መታወቂያ ወይም ፖስፓርት ይዞ መቅረብ*

አትሌቶች በስም ጥሪ ቦታ በዘመኑ በክልላቸው /ከተማ አስተዳደራቸው የታደሰ ቴሰራ ይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡ የግል ተወዳዳሪዎች ማንነታቸውንና እድሜያቸውን የሚገልጽ ስርዝ ድልዝ የሌለው መታወቂያ ወይም ፖስፖርት ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## *አንቀጽ ስምንት*

## *የመወዳዳሪያ ቁጥር*

ማንኛውም ተወዳዳሪ የመወዳደሪያ ቁጥሩን በደረትና በጀርባው ላይ በሚታይ መልኩ መለጠፍ አለበት፡፡ ያለመወዳደሪያ ቁጥር መወዳደር አይቻልም፡፡

## *አንቀጽ ዘጠኝ*

## *የውድድር አለባበስ*

ማንኛውም ተወዳዳሪ የክልሉን፣ የከተማ አስተዳደሩን፤ የክለቡንና የተቋሙን ማለያ ለብሶ መወዳደር አለበት፡፡ያለ ማለያ መወዳደር አይቻልም፡፡

## *አንቀጽ አስር*

## *የአትሌቱ ጤንነት*

በውድድሩ ተካፋይ የሚሆኑ አትሌቶች ጤንነታቸው የተሟላ መሆን አለባቸው፡፡ የጤንነት ችግር ያለባቸው አትሌቶች ተሰልፈው ቢገኙና ጉዳት ቢደርስባቸው ተጠያቂ የሚሆነው እራሱ ክልሉ/ ከተማ መስተዳድሩ /ክለቡ ወይም አትሌቱ ብቻ ይሆናሉ፡፡

## *አንቀጽ አስራ አንድ*

## *የሥነ-ሥርዓት ጉድለት*

ማንኛውም ተወዳዳሪ፣ አሰልጣኝ ፣ቡድን መሪ ፣አትሌት፣ ወጌሻ፣ ወይም የቡድኑ አባላት ወድድሩ በሚከናወንበት ወቅት የስነ-ስርዓት ጉድለት ካሳየና ውድድሩን በሚመሩ ዳኞችና የውድድር አመራሮች ሪፖርት ቀርቦ ጥፋቱ ከተረጋገጠ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በተዘጋጀው የአሠልጣኞች፣ አትሌቶችና የክለቦች የሥነ-ምግባር ደንብ መሠረት ይቀጣል፡፡

## *አንቀጽ አስራ ሁለት*

## *የቡድን ውጤት*

ተወዳዳሪ ቡድኖች ካስመዘገቡት አስራ ሁለት አትሌቶች ውስጥ ቀድመው ለገቡ አራቱ አትሌቶች ነጥብ ይሰጣል፡፡ በቡድን ነጥብ አሰጣጥ ከአነስተኛ ወደ ከፍተኛ ቁጥር የገቡበት ደረጃ ተደምሮ አነስተኛ ድምር ያስመዘገበ ቡድን አሸናፊ ይሆናል፡፡ የውጤት ድምራቸው እኩል ሲሆን መጨረሻ ነጥብ ያስመዘገበ /ዘጊው አትሌት/ ማለት በቡድኑ ቀድሞ ውድድሩን ላጠናቀቀ የቀረበው አትሌት ቡድን አሸናፊ ይሆናል፡፡

**ምሳሌ፡-**

- ቡድን “ሀ” 1ኛ፣ 5ኛ፣ 8ኛ፣ 9ኛ ቢወጡ ድምራቸው 23 ይሆናል፡፡
- ሁለቱ “ለ” 2ኛ፣ 3ኛ፣ 6ኛ፣ 12ኛ ቢወጡ ድምራቸው 23 ይሆናል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ቡድኖች ነጥባቸው እኩል ቢሆኑም ለአንደኛነት የቀረበው የመጨረሻ /ዘጊው አትሌት/ 9ኛ የወጣ የ “ሀ” ቡድን ስለሆነ የ “ሀ” ቡድን አሸናፊ ይሆናል፡፡
- ከአራት በታች ውጤት ያስመዘገቡ ቡድኖች የቡድን ድምር ውጤት ባይመዘገብላቸውም ባስመዘገቡት ውጤት አትሌቶቹ በግል ይሸለማሉ፡፡

## *አንቀጽ አስራ ሶስት*

## *ክስና አቤቱታ ስለማቅረብ*

1. የአትሌት ተገቢነት የክስ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው ውድድሩ ከመጀመሩ ቢያንስ ከ1 ሰዓት በፊት ነው፡፡ የውድድር ውጤቶችን በተመለከተ የውድድሩ ውጤት ይፋ ከተደረገ በኋላ በ30 ደቂቃ ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ የውድድር ዋና ዳኛ ውሳኔ መስጠት ወይም ጉዳዩን ከክስ ሰማ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ በዋና ዳኛው ውሳኔ ያልተስማማ ቡድን በጽሁፍ ከብር *300.00 /ሶስት መቶ ብር/* ጋር ለክስ ሰሚ ኮሚቴ ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ክሱ በክስ ሰሚ ኮሚቴ ተጣርቶ ተገቢ ክስ ሆኖ ከተገኘ የተያዘው ብር ተመላሽ ሆኖ ክሱ ተቀባይነት ይኖረዋል ፡፡ ነገር ግን ክሱ ተቀባይነት ካላገኘ የተያዘው ብር ለፌዴሬሽኑ ገቢ ሆኖ ውሳኔው የፀና ይሆናል ፡፡

# *አንቀጽ አስራ አራት*

## *ሽልማት*

1. በሁለቱም ጾታ ከ1ኛ-3ኛ ለሚወጡ አትሌቶች የሜዳሊያ ሽልማት ይሰጣል፤
2. በግል በሁለቱም ጾታ ከ1ኛ-6ኛ ለሚወጡ አትሌቶች የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል፤
3. ለቡድን አሸናፊዎች በሁሉቱም ጾታ የዋንጫ ሽልማት ይሰጣል፤

# *አንቀጽ አስራ አምስት*

## *የቴክኒክ ስብሰባ*

የቴክኒክ ስብሰባ ጥር 23/2012 ዓ.ም. ዓ.ም. ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ቢሾፍቱ ወጣት ማዕከለ ይካሄዳል፡፡ በቴክኒክ ስብሰባ ላይ ከእያንዳንዱ ቡድን አንድ ቡድን መሪና አንድ አሠለጣኝ ይገኛሉ፡፡

# *አንቀጽ አስራ ስድስት*

## *የክልሎችና የከተማ አስተዳድሮች ኮታ*

1. ለትግራይ ክልል 8 ሰው ቡድን መሪ እና አሰልጣኝ ጨምሮ፤
2. ለአማራ ክልል 8 ሰው  ቡድን መሪ እና አሰልጣኝ ጨምሮ፤
3. ለኦሮሚያ ክልል 8 ሰው  ቡድን መሪ እና አሰልጣኝ ጨምሮ፤
4. ለደቡብ ክልል 8 ሰው  ቡድን መሪ እና አሰልጣኝ ጨምሮ፤
5. ለሐረሪ ክልል 4 ሰው አሰልጣኝን ጨምሮ፤
6. ድሬደዋ አስተዳደር 4 ሰው አሰልጣኝን ጨምሮ፤
7. ለአዲስ አበባ ከተማ ስተዳደር 8 ሰው ቡድን መሪ እና አሠልጣኝ ጨምሮ
8. ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል 4 ሰው አሰልጣኝን ጨምሮ፤
9. ለጋምቤላ  ክልል 4 ሰው አሰልጣኝን ጨምሮ፤
10. ለአፋር ክልል 4 ሰው አሰልጣኝን ጨምሮ፤
11. ለሱማሌ ክልል 4 ሰው አሰልጣኝን ጨምሮ ሲሆን፤

    ነገር ግን ከተሰጠው ኮታ በተጨማሪ ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች ወጪያቸውን ሸፍነው የአትሌቶችን ቁጥር ጨምረው መሳተፍ ይችላሉ፡፡

# 13ኛው የኢትዮጵያ ግማሽ ማራቶን ውድድር

# የተወዳዳሪ አትሌቶች መመዝገቢያ ቅጽ

ክልል/ ከተማ አስተዳደር/ ክለብ ተቋም ______________________________

| ተ.ቁ. | ሴቶች | የትውልድ ዘመን |
|---|---|---|
| 1. | | |
| 2. | | |
| 3. | | |
| 4. | | |
| 5. | | |
| 6. | | |
| 7. | | |
| 8. | | |
| 9. | | |
| 10. | | |
| 11. | | |
| 12. | | |

| ተ.ቁ. | ወንዶች | የትውልድ ዘመን |
|---|---|---|
| 1. | | |
| 2. | | |
| 3. | | |
| 4. | | |
| 5. | | |
| 6. | | |
| 7. | | |
| 8. | | |
| 9. | | |
| 10. | | |
| 11. | | |
| 12. | | |

- የቡድን መሪ ሥም_______________
- የአሠልጣኝ ስም ___________________
- ወጌሻ___________________________

<u>ቅጹን የሞላው</u>

- ስምና ፊርማ _____________
- ኃላፊነት ____________
- ቀን ______________

# 13ኛው የኢትዮጵያ ግማሽ ማራቶን ውድድር ኘሮግራም

ቀን፡ - ጥር 24/2012

ቦታ፡- በኦሮሚያ ክልል ቢሾፍቱ

| ተ.ቁ | ሰዓት | ክንውን | አፈፃፀም |
|---|---|---|---|
| 1. | 1፡00 | የውድድሩ ስፍራ ለተመልካቾች ክፍት ይሆናል | በውድድር አስተናጋጅ |
| 2. | 1፡15 | የሴት ተወዳዳሪዎች ስም ጥሪ ይደረጋል | በስም ጠሪ ዳኞች |
| 3. | 1፡30 | የወንድ ተወዳዳሪዎች ስም ጥሪ ይደረጋል | በስም ጠሪ ዳኞች |
| 4. | 1፡45 | የሴቶች ውድድር ይጀመራል | በአስነሺ ዳኞች |
| 5. | 2፡00 | የወንዶች ውድድር ይጀመራል | በአስነሺ ዳኞች |
| 6. | 4፡00 | ለአሸናፊ አትሌቶች የሜዳሊያና የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል | በተጋባዥ እንግዶች |
| 7. | 4፡20 | ለአሸናፊዎች የዋንጫ ሽልማት ይሰጣል | በዕለቱ የክብር እንግዳ |
| 8. | *4፡30* | *የውድድሩ ፍፃሜ ይሆናል* | |

*የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን*